## በቤት ውስጥ መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

- በኢቦላ በሽታ የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰውን በተቻለ መጠን ለብቻው በተዘጋጀ ቦታ መለየት አለበት፡፡
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰውን ወደ ጤና ተቋማት በምንወስድበት ወቅት ከታማሚው ጋር አላስፈላጊ ንክኪ መደረግ የለበትም፡፡
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰውን ወይም የሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪ ከተፈጠረ ወዲያውኑ እጃችንን በውሃና በሳሙና መታጠብ አለብን፡፡
- በኢቦላ በሽታ የተጠቃውን ሰው በምንረዳበት ወይም በምንከባከብበት ጊዜ የእጅ ጓንት፣ የአይን መከላከያ መሳሪያ (ጎግል)፣ የፊት መሸፈኛ እና ሌሎች የሰውነት መከላከያ መሳሪያዎች መጠቀም አለብን፡፡
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰው የሰውነት ፈሳሽ መሬት ከበከለ በረኪና ይጨምሩበት፤ ከ15 ደቂቃ በኋላም ይፀዳ፤ በቆሻሻ የተነካኩ ቁሳቁሶችና ልብሶች መቃጠልአለባቸው፡፡
- በኢቦላ በሽታ ታሞ የሞተ ሰው የቀብር ስነስርዓት ስናከናውን ከአስከሬን ጋር ንክኪ አለማድረግ፣ የጋራ እጅ መታጠቢያ አለመጠቀም፡፡
- የቀብር ስነስርዓት ሲፈፀም አስከሬኑ በፕላስቲክ ከረጢት መጠቅለል አለበት፡፡ የቀብር ስነስርዓቱም በሰለጠነ የጤና ባለሙያ ምክር መታገዝ አለበት፡፡

## ነፃ የስልክ መስመር 8335

## ለተጨማሪ መረጃ በሚከተሉት ይጠቀሙ

**የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ማዕከል**
**ሥልክ ፡** +251 11 213 8298
+251 11 276 5340
**ፋክስ ፡** +251 11 275 8634
**ኢሜል ፡** ephi@ethionet.et
**ድረ-ገጽ ፡** http://www.ephi.gov.et

# ኢቦላ ቫይረስ በሽታ

"ኢቦላ በፍጥነት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው። ይሁን እንጂ በሽታውን መከላከል ይቻላል"

ለተጨማሪ መረጃ በሚከተሉት ይጠቀሙ
የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ማዕከል
ሥልክ፡ +251 11 213 8298

በኢፌድሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
**የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ማዕከል**

## የኢቦላ በሽታ ምንድ ነው?

የኢቦላ በሽታ በቫይረስ አማካኝነት የሚመጣ እና በፍጥነት ከሰው ወደ ሰው በመተላለፍ በበሽታው ከተያዙት ውስጥ 90 በመቶ የሚደርሱትን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፡፡ በሽታው ሰውን ብቻ ሳይሆን እንደ ጦጣ፣ ዝንጀሮና ገመሬ ዝንጀሮ ያሉ እንስሳትንም የሚያጠቃ ነው፡፡ የኢቦላ በሽታ በወረርሽኝ መልክ የተከሰተው እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ1976 ሲሆን፤ ይኸውም በዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ ኮንጎ ውስጥ ኢቦላ በተሰኘ ወንዝ አካባቢ በሚገኝ አንድ መንደርና በሱዳን ገጠራማ አካባቢ ነው፡፡ የቫይረሱ ምንጭ ምን እንደሆነ እስካሁን በውል ባይታወቅም ባሉ ማስረጃዎች ላይ በመንተራስ ግን በሽታው መጀመሪያ የሌሊት ወፍ ላይ እንደተከሰተ ይታመናል፡፡

አሁን የተከሰተው የኢቦላ ወረርሽኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአለም ጤና ድርጅት ሪፖርት የተደረገው መጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ.ም በጊኒ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አማካኝነት ነው፡፡ ከዚያም በኋላ በሽታው ወደ ላይቤሪያ፤ ሴራ ሊዮን እና ናይጄሪያ በመዛመቱ ሐምሌ 18 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ 1201 ህመም እንዲሁም 672 ሞት ተመዝግቧል፡፡ የኢቦላ በሽታ በቫይረስ የሚመጣ ገዳይ በሽታ ነው፡፡ በሽታው በፍጥነት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት የሚዳርግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሽታውን መከላከል ይቻላል፡፡

## የኢቦላ በሽታ እንዴት ይተላለፋል?

- ከታመመው ሰው ቁስል፣ ደም፣ ምራቅ፣ ትውከት፣ አይነምድርና ሽንት ጋር በቀጥታ በመነካካት ወይም እነዚህ ፈሳሾች ወደ ጤነኛ ሰው አይን ተረጭተው ከገቡ፣
- ከህመምተኛው ሰው በወጣ ፈሳሽ የተበከለ ጨርቅን በመጠቀም፣
- ንጽህናቸው ባልተረጋገጠ ወይም ሌሎች ህሙማን የተጠቀሙበትን መርፌ ሳይቀቅሉ በመጠቀም፣
- የኢቦላ በሽታ ታማሚ የተጠቀመበትን መርፌና ስለት ያላቸውን መሳሪያዎች በመጠቀም፣
- በኢቦላ በሽታ የሞተ ሰውን አስከሬን በቀጥታ በመነካካት፣ በኢቦላ በሽታ የሞተውን እንስሳ ስጋ በመመገብ ናቸው፡፡

## ታማሚው የህክምና እርዳታ ማግኘት ያለበት መቼ ነው?

አንድ ሰው የኢቦላ በሽታ በተከሰተበት አካባቢ ከነበረና በኢቦላ በሽታ ከተያዘ ወይም ከተጠረጠረ ሰው ጋር ንክኪ ፈጽሞ ከሆነ በአፋጣኝ የህክምና እርዳታ ማግኘት አለበት፡፡ ሰዎችን ከበሽታው ለመታደግም አስቸኳይ ህክምና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ የበሽታውን መስፋፋት የመግታት እርምጃና በሽታውን የመከላከል ሂደቶችም የግድ በአፋጣኝ ሊከናወኑ ይገባል፡፡

## የኢቦላ በሽታ ምልክቶች ምንድናቸው?

በኢቦላ በሽታ የተጠቃ ሰው በመጀመሪያዎቹ ቀናት ከፍተኛ የሆነ እና ድንገተኛ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ከፍተኛ የድካም ስሜት እና ራስ ምታት ይታይበታል፡፡ ከዚያም የቆዳ ሽፍታ ይከተላል፡፡ ከነዚህ ምልክቶች በኋላም ማስመለስ/ትውከት፣ የሆድ ህመም፣ የጉሮሮ ህመም እና የተቅማጥ ህመም ያስከትላል፡፡ እነዚህ ምልክቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ በመባባስ ወደ ጉበት ህመም፣ ክብደት መቀነስ፣ መቃዠት፣ የኩላሊትና የሳንባ ህመም ሲሸጋገሩ አንዳንድ ጊዜም ከሁሉም የሰውነታችን ክፍት ቦታዎች ደም መፍሰስ እና የዋና ዋና የሰውነታችን አካላት በአንድ ጊዜ ሥራ ማቆም ሊከሰት ይችላል፡፡

አንድ ሰው በኢቦላ በሽታ አምጪ ተሕዋስ ከተለከፈበት ጊዜ ጀምሮ ምልክቱ እስከሚታይበት ጊዜ ድረስ የሚወስድበት ጊዜ ከ 2 እስከ 21 (በአመዛኙ ከ8 እስከ 12) ቀናት አይበልጥም፡፡ በሽተኛው ከላይ የተጠቀሱትን ምልክቶች ካሳየበት ጊዜ ጀምሮ በሽታውን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በበሽታው ተይዞ ምልክቶቹን ማሳየት ባልጀመረባቸው ቀናት በሽታው አይተላለፍም፡፡

## በኢቦላ በሽታ መያዙ የተጠረጠረ ወይም የተያዘ ሰው ካገጠመን ምን ማድረግ አለብን?

- ታማሚውን በምንረዳበት ጊዜ ሰውነታችንን ከበሽታው መከላከል የሚያስችለንን የእጅ ጓንት፣ የአይን መከላከያ መሳሪያ (ጎግል) እና የአፍንጫና የአፍ መሸፈኛ ማስክ መጠቀም አለብን፤
- የታመመው ሰው ወዲያውኑ ለአስፈላጊ ህክምናና እርዳታ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ጤና ተቋም መወሰድ አለበት፤
- ማንኛውም በኢቦላ በሽታ የተጠረጠረ ሰው በሚገኝበት ወቅት ወዲያውኑ በአቅራብያው ወደሚገኘው ጤና ተቋም ወይም ጤና ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለብን፡፡
- በበሽታው መያዙ የተጠረጠረ ወይም የታመመ ሰው የተጠቀመበት አልባሳትና መኝታውን በበረኪና ማጠብ ይኖርብናል፡፡

## ለኢቦላ በሽታ ተጋላጭ የሆኑት እነማን ናቸው?

የኢቦላ በሽታ ከታመመ ሰው የሚወጣውን ደምና ሌሎች የሰውነት ፈሳሾች ጋር በቀጥታ በመነካካት የሚተላለፍ በመሆኑ ከታመመው ሰው ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው በበሽታ ሊያዝ ይችላል፡፡ በሽተኛውን በምንመግብበትና በምንከባከብበት ጊዜ የእጅ ጓንትና ሌሎች መከላከያ መሳሪያዎች ሳያደርጉ ከሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪ የሚፈፅሙ ከሆነ በቀላሉ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ፡፡

በኢቦላ በሽታ የሞተውን ሰው አስከሬን ያለ እጅ ጓንትና ሌሎች የመከላከያ መሳሪያዎች የምንነካካ ከሆነ በቀላሉ በበሽታው ልንጠቃ እንችላለን፡፡

## የኢቦላ በሽታን እንዴት ልንከላከል እንችላለን?

- የእጅ ጓንት፣ የአይን መከላከያ መሳሪያ (ጎግል) እና ሌሎች የሰውነት መከላከያ መሳሪያዎችን በመጠቀም በበሽታው ከተጠቃ ሰውነት ውስጥ ከሚወጣው ማንኛውም ፈሳሽ ጋር በቀጥታ ባለመነካካት፣
- ያለ እጅ ጓንት በበሽታው የተጠቃውን ሰው ቁስል አለመንካት፣
- በኢቦላ በሽታ የተያዘው ሰው የተጠቀመውን መርፌና ሌሎች ስለት ያለቸውን መሳሪያዎች አለመጠቀም፣
- በኢቦላ በሽታ መያዙ የተጠረጠረና የሞተ እንስሳን ስጋ አለመመገብ፣
- የኢቦላ በሽታ ስርጭትን ለመግታት በኢቦላ በሽታ የሞተውን ሰው አስከሬን በምንነካበት ጊዜ ጓንትና ሌሎች የመከላከያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ሰውነታችንን ከየትኛውም የሰውነት ፈሳሽ ንክኪ መከላከልና የቀብር ስነስርአትም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈፀም ማድረግ ፤ እንዲሁም ከቀብር በኋላ ያለውን ስነስርዓት ማሳጠር፣
- የታመመውን ሰው ከረዳን ወይም በኢቦላ በሽታ የሞተውን ሰው አስከሬን ከነካን በኋላ እጃችንን በውሃና በሳሙና በደንብ መታጠብ አለብን፡፡